**በተለያዩ ምክንያቶች ከቀያቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች እየተሰጠ ያለውን የጤና አገልግሎት አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ**

1. **የመግለጫው ዋና ዓላማ፡-**
   - ለመገናኛ ብዙሃን በሀገር ውስጥ ተፈናቅለው በተለያዩ መጠለያ ጣቢያዎች ስለሚገኙ ወገኖች የጤና ሁኔታ እና እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን በተመለከተ በየሳምንቱ በቋሚነት መግለጫ በመስጠት ለህብረተሰቡ በቂ እና ወቅታዊ መረጃ እንዲኖራቸው እንዲሁም በጤናው ዘርፍ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት ነባራዊ ሁኔታዎችን በመረዳት ተገቢውን እገዛ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ነው፡

2. **ለተፈናቃይ ወገኖች የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶችን በተመለከተ፡-**

   - እስካሁን ባለን መረጃ መሰረት 758 480 ተፈናቃዮች ወደ መኖሪያ ቀያቸው የተመለሱ ሲሆን ተፈናቃዮችን ወደ መኖርያቸው የመመለሱ ሂደት እንደቀጠለ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ ተመለሻች በሚገኙባቸው አከባቢዎች የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ከክልሎች ና ከአጋር አካላት ጋር አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል።

   - ተፈናቃይ ወገኖች በሚገኙባቸው ክልሎች በአጠቃላይ ከ650 በላይ የጤና ባለሙያዎች በማሰማራት ድጋፍ ተደርጓል።

   - በደቡብ ክልል በጌዲኦ ዞን ለሚገኙ ተፈናቃዮች ከሌሎች የጤና አገልግሎቶች በተጨማሪ የስነ አእምሮ ህክምና በመሰጠት ላይ ሲሆን በአጠቃላይ ከ 660 በላይ ሰዎች ታክመዋል። አገልግሎቱን በሌሎች ተፈናቃዮች በሚገኙባቸው ክልሎች ለማስፋፋት እንዲቻል ለአማራና ለሶማሌ ክልል የጤና ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል።

   - በሶማሌና በደቡብ ክልል በአተት በሽታ ምልክቶች የተጠረጠሩ ታካሚዎች የነበሩ ሲሆን ከአለም የጤና ድርጅት ጋር በመተባበር በሽታውን ለመመርመር የሚያስችሉ መስሪያዎች እንዲሁም በሽታው ቢከሰት ለ210 ሺህ ሰዎች ሕክምናውን ለመስጠት የሚያስችሉ መድሐኒቶች ወደ ክልሎቹ ተልኳል። ይሁንና በአሁን ወቅት ምንም አይነት የአተት ወረርሽኝ አልተከሰተም።

   - በደቡብ ክልል 210,000 ተፈናቃዮችን ማከም የሚስችሉ የጤና መድሃኒቶች ግብአቶች በክልሉ የመድሃኒት ማከማቻ በተጠባባቂነት እንዲቀመጥ ተደርጓል።

   - በቤ/ጉሙዝ ክልል ከማሺ ዞን በግጭቱ ምክንያት የጤና ባለሙያዎች ለቀው በመውጣታቸው እና ጉዳት የደረሰባቸው የጤና ተቋማት በመኖሩ አገልግሎት የሚሰጡ የጤና ተቋማት ቁጥር እጅግ አናሳ ነው። በዞኑ ከሚገኙ 39 የጤና ተቋማት 11 ጉዳት ና ዘረፋ ደርሶባቸዋል። በተጨማሪም ከ 227 የጤና ባለሙያዎች ውስጥ 115ቱ ለቀው ወጥተዋል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ የጤና ባለሙያዎች ወደ በታው መላክ ተጀምሯል።

- **በአጠቃላይ በዚህ አመት ተፈናቃይ ወገኖች ለሚገኙባቸው ክልሎች 528 ሚሊዩን ብር በላይ ወጪ ሆኗል።**
-

## 3. ተፈናቃይ ወገኖች በተመለከተ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- ተመላሽ ወገኖች በሚገኙባቸው አከባቢዎች የጤና አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት እጥረት መኖሩ

- በአጠቃላይ ተፈናቃይ ወገኖች በሚገኙባቸው ክልሎች ከፍተኛ የሆነ የጤና ባለሙያዎች እጥረት መኖሩ ከዚህም ጋር በተያያዘ በጎ ፈቃደኞች በተቋሙ ማበራዊ ገፅ ላይ ከነገ ጀምሮ እንዲያመለክቱ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

- ተፈናቃይ ወገኖች በሚገኙባቸው አከባቢዎች ለወረርሽኞች ተጋላጭ መሆናቸው

- ከወቅቱ ዝናብ ጋር ተያይዞ የመንገድ ችግሮች ማጋጠማቸው

## 4. የሀገራችን ሌሎች የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ወቅታዊ ሁኔታ፦

- **ኩፍኝ**፦ በኦሮሚያ ክልል እ.አ.አ ከጥር 1 ጀምሮ እስከ አለፈው ሳምንት ድረስ በአጠቃላይ 3611 በበሽታው የተያዙ ሲሆን በተሰጠው ክትባት አማካይነት የበሽታው ተዛማችነት የቀነሰ ቢሆንም በሮቤ ከተማ እንደቀጠለ ነው። በተጨማሪም በሶማሌ ክልል ከታህሳስ ወር ጀምሮ በበሽታው የተያዙ ቁጥር 1470 ደርሷል። ክትባት በተሰጠባቸው ቦታዎች ተዛማችነቱ የቀነሰ ቢሆንም በሸበሌና በጀራር ዞኖች ግን በሽታው እንደቀጠለ ነው። ለሁለቱም ክልሎች ክትባት ለመጀመር የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት በዚህ ሳምንት ይጠናቀቃል።
- **ችኩንጉኒያ**፦አፋር ክልል አዳር ወረዳ በኢልውሃ ከተማ የተከሰተው የችኩንጉኒያ ትኩሳት በሽታ ከየካቲት 29 እስከ ሚያዚያ 14/2011 ባለው ጊዜ ውስጥ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር በድምሩ አንድ ሺህ አንድ መቶ አስራ ስምንት (1118) ደርሷል። ሆኖም ከባለፉት ሳምንታት ጋር ሲነፃፀር አዲስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር በእጅጉ ቀንሷል።

ሚያዝያ 16 ቀን 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ